## የጽ/ቤቱ ዓመታዊ ሪፖርት

ሪፖርት ላኪ

ዞን -----------------

ወረዳ ኮንታ ልዩ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት

ቀበሌ ------------------

ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ ከ1/11/2000-30/07/2001 ዓ/ም

**<u>የታቀዱ ተግባራት</u> :-**

## 3.1 ቁልፍ ተግባራት

1. የልዩ ወረዳው የሪፎርም አስፈፃምና አስቀጣይ ተቋም በ20 ጽ/ቤቶች የተፈጠረ የማስፈፀም አቅም
2. የተቀናጀ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ትግበራ ስርዓት
3. የወረዳውን የፍትህ ስርዓት ስኬታማ ለማድረግ የተፈጠረ የተቋም አቅም
4. የመልካም አስተዳደር ስርዓት የዘረጉ 75% ቀበሌዎች
5. አይሲቲ /ICT / መጠቀምን በተመለከተ

**<u>የታቀዱ ዝርዝር ቁልፍ ውጤቶች</u>:-**

1. በርቀት ትምህርት ደረጃዎች ያሻሻሉ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች
2. ለሠራተኞች ተከታታይነት ያለው የአጭር ጊዜ የሀገር ውስጥ የሥራ ላይ ስልጠና እድል መስጠትና ማብቃት ፣
3. የህዝብ አገልጋይነት ስሜት ፣ቁርጠኝነት ፣የውስጥ ተነሳሽነት እንዲፈጠር ተከታታይ የህዝብ ግንኙነት ሥራ መስራት ፣
4. አመራሩ የሪፎርሙ ባለቤት እንዲሆኑ ግንዛቤ መፍጠር
5. ሁሉም የሪፎርም ፕሮግራም በቅንጅት ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስልት መቀየስ
6. በልማት ዕቅዶች አተገባበር የበላይ አመራሮች ተጠያቂ የሚሆንበትን አሰራር ማስፈን፣
7. የሪፎርም ፕሮግራሞችን ውጤታማ በሆነ መልኩ አቀናጅቶ ያልተገበሩ አመራሮችን በይፋ ተጠያቂ የሚሆኑበትን አሠራር ማስፈን፣
8. ቀበሌዎች የወረዳ አመራሮችና ባለሙያዎችን በአጫጭር ስልጠና ማብቃት፣
9. አዳዲስ የአሰራር ሥርዓቶችን የሚገልፁ ማኑዋሎችን ማስራጨትና ስለተግባራነዊነታቸው መከታተል ፣
10. በወረዳ ደረጃ ሊደረግ የሚገባውን ዝቅተኛ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲዘጋጅ በማድረግና ህ/ሰቡ እንዲያቀው ማደረግ ፣

11.የወረዳ መረጃ መረብ ማጠናከርና ማጎልበት፣

12.የሴክተር መ/ቤቶች በLAN በማገናኘት ፈጣን የመረጃ ፍሰት ልውውጥ እንዲፈጠር ሁኔታ ማመቻቸት፣

13.የክረምት ትምህርት የሥራ ላይ የሙያ ትምህርት ደረጃ ማሻሻያ እድል መስጠት/ዲፕሎማና ዲግሪ/፣

14.መሠረታዊ የሥራ ሂደት ባጠናቀቁት 7 ሴክተሮች ወደ ሙሉ ተግበራ ማሻጋገርና ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ ሥርዓት መዘርጋት ፣

15.በወረዳው በሁሉም ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና ሥርዓት፣

16.በወረዳው የፍትህ ስርዓት መሻሻያ ፕሮግራሞችን ስኬታማነትና ውጤታማ በማድረግ የፍትህ አካላትን በስልጠና ማብቃት፣

17.መሠረታዊ የአሰራር ሥርዓት /BPR/ በተገበሩት የሥራ ሂደቶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች መደገፍ ፣

- ሰባት ሴ/መ/ቤቶች የስራ ሂደቱን በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ለማቀላጠፍ የተሰጠ ድጋፍ/LAN/
- አግልገሎት መሰጠት የቻለ መረጃ ማዕከል

18.የኢንፎርሜሽን ኮሚንከሽን ቴክኖሎጅን መሠረተ ልማት ማስፋፋትና በዘርፉየሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የተሰጠ ስልጠና

19.የኢንተርኔት አገልግሎት ያገኙት መ/ቤቶችና የመ/ሠራተኞች ፣

- በዘመናዊ መረጃ ማስተላለፍ /E-mail/ ሥራ የሰለጠኑ የቀበሌ መረጃ ሠራተኞችና የወረዳ ባለሙያዎች ፣
- አድቫንስ የኮምፒውተር ኢንቴርነት ስልጠና ያገኙ 20 የወረዳ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች
- በመሠረታዊ የኮምፒውተር ኢንተርኔት የሰለጠኑ 17 ባለሙያዎችና ኃላፊዎች

## <u>የተፈጸሙ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት</u>

1. በ2001 ዓ/ም የሚሰጠውን የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የርቀት ትም/ት ዕድል ለ4 ባለሙያዎች የተሰጠ ሲሆን እድሉን ያገኙት ትም/ቱን ለመጀመር በመጠባበቅ ላይ ይገኛል ፡፡

- በ2002 በመደበኛ የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ፕሮግራም መረሃ-ግብር ለሚገቡ ሁለት/2/ እጩ ተፈታኞችን በማወዳደር ለክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ አስተላልፈና፡፡

2. በ2002 በመደበኛ ትምህርት በአርባን ኢንጅነሪንግ ለሚገቡ 5 እጩዎችን መልምለን ለክልል አቅም ግንባታ አስተላልፈናል ፡፡
3. በ2ኛ ድግሪ በ2002 በመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም Development Economics,public financial Management ,law በያንዳንዱ የሙያ መስመር 1 እጩ በድምሩ 3 ወንድ እጩዎችን መልምለን ለክልል አቅም ግንባታ በመላክ የመግቢያ ፈተና ወስደው ዉጤት በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡
4. በሁሉም የሪፎርም ፕሮግራም በቅንጅት ተግባራዊ እንዲሆን በ8/12/2000 ዓ/ም ከ13 ሴክተር መ/ቤቶች የሪፎርም አስፈፃሚ የፍሽሮች ጋር የጋራ መግባባት ተደርሷል
    - የ2000 ዓ/ም የ2ኛ ዙር የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈፃፀም ምዘና በተመለከተ
    - የ2000 ዓ/ም የ1ኛ ዙር የውጤት ተኮር እቅድ ዝግጅት በተመለከተ
    - በየሴክተሩ የአገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል ፡፡
    - ለወደፊቱም ሁሉም የሪፎርም ፕሮግራሞች በቅንጅት ተግባራዊ ስለመሆናቸው የመ/ቤቱ አፍሰሮች በቅንጅት ተግባራዊ ስለመሆናቸው የመ/ቤቱ ኦፊሰሮቹ በየወሩ በየሩብ ዓመቱ እየተገናኙ ውይይት ለማድረግ ተወስኗል ፡፡
    - በሴክተሩ የተገልጋዮችን የአስተያየት መስጫ መዝገብና የሀሣብ መስጫ ሣጥንን በማየት ለተገኙት አስተያየቶችና ጥቆማዎች በወቅቱ ምላሽ እንዲሰጥበት ተደርጓል ፡፡
5. በአመቱ ውስጥ በወረዳው በተለያዩ ሴ/መ/ቤቶች ወንድ 107 ሴት 84 ድምር 191 ሠራተኞች በተለያየ ጊዜያት የተሰጠውን የሀገር ውስጥ አጫጭር የሥራ ላይ ስልጠና መረጃ ከየሴክተሩ የማሰባሰብ ሥራ ተሰርቷል ፡፡
6. በክረምት የሥራ ላይ የሙያና የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ እድል መረጃ ከየሴክተሩ በዲፕሎማ መረሃ-ግብር ወንድ 21 ሴት 11 በድምሩ 32 በዲግሪ መረሃ -ግብር ወንድ 14 ሴት 5 ድምር 19 በአጠቃላይ የ51 ሠራተኞች የማሰባሰብ ሥራ ተሰርቷል ፡፡

7. የሪፎርሙ ፕሮግራሞ ውጤታማ በሆነ መልኩ ተቀናጅተው በየሴክተሩ እንዲተገበሩ በየወሩና እንደአስፈላጊነቱ ከአመራሩ /የቢሮ ኃላፊዎች ጋር በመገናኘትና በመወያየት ችግሮችን በመፍታት እየተሰራበት ይገኛል ፡፡
8. አመራሮች /ኃላፊዎችን የሪፎርም ባለቤት ከማድረግ አኳያ በየወሩ በየመ/ቤቱ በመገኘት በ5 ንዑሣን ፕሮግራሞች አፈፃፀም ዙሪያ ያሉት ጠንካራ አሰራሮች እንዲጎለብቱ ደካማ አሰራሮች እንዲሻሻል አመራሮችን የሪፎርሙ ባለቤት በመሆን በግንባር ቀደም ማንቀሳቀስ እንዳለባቸው በ18 መ/ቤት የጋራ ውይይት ተካሂዷል ፡፡
9. የህዝብ አገልጋይነት ስሜት ቁርጠኝነትና የውስጥ ተነሳሽነት እንዲፈጠር በየሴክተሩ ከሪፎርሙ የሥራ እንቅስቃሴ ጋር በማያያዝ እንዳስፈላጊነቱ ድጋፍ፣ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ተሰርቷል፡፡
10. በዓመቱ ከደ/ክ/ሲ/ሰ/ኤጀንሲ የተላከውን የመንግስት መ/ቤቶችና ሰራተኞች የሥራ ቦታዎች የኤች አይቪ አድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ ለ19 ሴክተር መ/ቤቶች ተሰራጭቶል ፡፡
11. በልማት ዕቅዶች አተገባበር የበላይ አመራሮች በስትራቴጅክ ዕቅድ አተገባበር ዙሪያ ኃላፊነታቸውን የሚወጡበት ክትትልና ድጋፍ ለ13 ጽ/ቤቶች ተሰጥቷል ፡፡
12. በመሰረታዊ የስራ ሂደት ምደባ ያለገኙት ሰራተኞች በትምህርትና በጡረታ በመለየት የተላለፉ መመሪያዎቹን ለሴክተሮች እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ ምደባ ያለገኙት ሰራተኞች መረጃ የሚጠየቅ ሰንጠረዥ ለሴክተሮች ተበትኖ መረጃው ተጠናቅረው ለክልል አቅም ግንባታ ቢሮ ተላልፈዋል፡፡
13. ለፀሐፊዎችና ሾፌሮች ተሻሽለው የተላከው መመሪያ ለሴክተሮች እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡
14. በልዩ ወረዳው የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ትግበራ (BPR ) ለተገበሩ ሰባት ሴክተር በመ/ቤቶች በተቀመጠላቸው እስታንዳርድ /standard/መሰረት ትግበራውን እየፈፀሙ መሆናቸውን ክልል አቅም ግንባታ ቢሮ በተላከልን ቼክ ሊስት መሰረት በማድረግ በለውጥ ፕሮግራሞች ጥናት መሰረት የክፍተት መለየትና መሙላት እንዲሁም ክትትል የማድረግ ስራ በተገባ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡
15. በአዲስ የሥራ ሂደት ልውጥ (BPR ) ወደ ሙሉ ተግበራ ለሚገቡ ለ7 መ/ቤቶች ከክልል የተላለፈውን መዋቅር ተግባራዊ እንዲያደርጉ ክትትል ተደርጓል ፡፡
16. በወረዳ ደረጃ ሊደረግ የሚገባውን ዝቅተኛ አገልግሎት አሰጣጥ እንደየመ/ቤቱ የሥራ ባህር በ3 ጽ/ቤቶች ተዘጋጅተው ለተገልጋዩ ግልጽ በሆነ ቦታ ላይ ተለጥፏል ፡፡

17. በዘመናዊ እንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ለማቀላጠፍ የተደረገ ድጋፍ /በLAN/ የአሰራር ስርዓት የተቀላጠፍ ለማድረግ ከሴክተሮች በቀረብልን የሙያ ድጋፍ ለአስተደደር ጽ/ቤትና በደኢህዴንቅ/ጽ/ቤት የdial up connection የኔትወርክ ዝርጋታ በማከናወን አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

18. በቀበሌዎች ፣ወረዳ አመራሮችንና ባለሙያዎችን ከማብቃት አንፃር በ3 ቀበሌዎች ቅድመ ስልጠና ዝግጅት ተደርጓል ፡፡

- በ22 በቀበሌዎች ለ40 የቀበሌ ሊቀመንበርና ሥራ አስኪያጆች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የስልጠና ርዕሶች ፡-

- በልማት ዕቅዶች አተገባበርና አዘገጃጀት
- በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞች እና
- ለቀበሌ ሥራ አስኪያጆች የተሃድሶ ስልጠና ለ2 ቀን በተለያዩ ሁለት ክላስተሮች የተሰጠ መሆኑን እንገልፃለን ፡፡

19. በጭዳ ዙሪያ ከ25/9/2001 -26/9/2001 ዓ.ም ድረስ ለ15 የቀበለ ስራ አስኪያጆች የአቅም ግንባታ ስልጠና ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ርዕሶች ላይ

- በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ
- መሪነት /leadership/
- በመረጃ አያያዝ በአጠቃላይ ለሁለት ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

20 በወረዳ ደረጃ ለሚገኙ ከፍተኛ አመራር መሠረታዊ የኮምፒዩተር ስልጠና ለ2 ሴቶችና ለ18 ወንዶች በድምሩ 20 ሰልጣኞች የአንድ ወር ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡

21 ለ15 ቀን ከ2/6/2001-17/6/2001 ዓ.ም መሰረታዊ የኮምፒውተር ስልጠና የወሰዱ የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ለተገበሩ ሴክተር መ/ቤት ባለሙያዎች ወ 9 ሴ4 በድምሩ 13 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

22 የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራሞች ስኬታማና ዉጤታማ ለማድረግ የፍትህ አካላትና በይበልጥ የማህበራዊ ፍርድ ሸንጎች በተለያዩ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያላቸውን ክፍተት በመለየት የመሙላት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

- የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅ ፈጣንና ፍታሀዊ አገልግሎት ለመስጠት ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት ለህብረተሰብ የተፋጠነ አገልግሎት እንዲዳረስ ተደርጓል፡፡
- የኮሚኒተህ ፖሊስንግ ለህብረተሰቡ በየቀበሌው በተመደቡ የፖሊስ ኦፊሰሮች በማስተማር ህብረተሰቡ ወንጀል ከመፍጠሩ በፍት በጋራ በመከላከል ወንጀለኞችን ለመቀነስ ተችሏል፡፡

## ያልተፈፀሙ ዝርዝር ቁልፍ ውጤቶች

- ❖ የወረዳ መረጃ መረብ ማጠናከርና ማጎልበት
- ❖ የዉጤት ተኮር /BSC/ዕቅድ አፈጻጸም ሥርዓት ትግበራን በመከታተል በታቀደው መሰረት እንዳይፈፀም ያደረገው በጥናቱ በመዘገየት ምክንያት ነዉ፡፡

## የታቀዱ አብይት ዝርዝር ውጤቶች

1. የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞ የአፈፃፀም ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ የተዘረጋ ሥርዓት
2. የተዘረጋ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ሥርዓት
3. በአንድ ቀበሌ የተዘረጋ የህብረተሰብ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት
4. በፀረ-ኤች አይቪ ኤድስ እንቅስቃሴ ለማጠናከር የቫይረሱ ሥርጭት ለመግታት በወረዳው ለሚደረገው ጥረት የተደረገ ድጋፋዊ እገዛ ፣
5. በአቅም ግንባታ እቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም እንዲካተቱ ያደረገ የሥርዓተ-ጾታ እቅድ
6. በጽ/ቤቱ ላይ የሚገኙ ሠራተኞችና አመራሮች ስርዓተ-ፆታና ኤች አይ ቪ ኤድስ የሚሰጥ ስልጠና
7. በጠቅላላ አገልግሎት እቅድ ተግባራዊ ማድረግ
8. በስራ አመራር ቁልፍ ሥራዎች የሴቶችን ተሳትፎ የሚያበረታታ ሥርዓትና አመራር መፍጠር ፣
9. በሲቪል ሰርቪስና በፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞችን የሴቶችን ተሣትፎ ለማሻሻል መስራት ፣

## የተፈፀሙ ዝርዝር ዓብይት ውጤቶች፡-

1. የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞ አፈፃፀም ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ በ13 ሴክተር መ/ቤቶች በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ፣በመልካም አስተዳደር ፣በፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም አፈፃፀም ላይ ሴክተሮች ሚያሳዩትን እንቅስቃሴን ለማጎልበት ክትትልና ድጋፍ ተደርጎል ፡፡
2. የተዘረጋ የእንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ አጠቃቀም ስርዓት ከማጎልበት አንፃር
   - ❖ የኢንቴርንት አገልግሎት በወረዳው ለሚገኙ ወ 3 ሴ- በድምሩ 3 ባለሙያዎች ወቅታዊ የሆኑትን መረጃዎችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጽ/ቤታችን የበኩሉን አስጸዋዖ አደርጓል ፡፡
   - ❖ በቪዲዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት የልዩ ወረዳችን ጤና ጥበቃ ባለሙያዎች ከቤንች ማጂ ዞን ሸኮ ወረዳ ጤና ኤክስቴንሽኖች ጋር የሥራ ልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡

- ❖ ከወረዳችን ን/ኢ/ጽ/ቤት ባለው የኢንተርፕራይዞች ልማት ስራ ሂደት ባለቤቶች ከጉራጌ ዞን ኤዣ የ ወረዳ የኢንተርፕራዞች ልማት ስራ ሂደት ባለቤቶች ጋር ልምድ ልዉዉጥ ተደርጓል፡፡
- ❖ የIBX ሲሰተም የወረዳው ፋ/ኢ/ልማት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተግባራዊ እንዲያደርጉ የIBXሲስተምን በICT ማዕከል በመዘርጋትና በIBX ላይ የሚሰሩት ሰራተኞች ሙያዊ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ❖ በወረዳው ውስጥ በሚገኙ ት/ቤቶችን የስኩልኔትና ኮምፒውተር ብልሽቶችን በመጠገንና ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ❖ በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ 44ቀበሌዎች ውስጥ ለ13 ቀበሌዎች የገመድ አልባ ስልኮች አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆኑ 1ቀበሌ ብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠቱን ያቋረጠ መሆኑን ለሚመለከተው ከፍል ሪፖርት በማድረግ ምላሽ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

3. በወረዳ ሴ/ር መ/ቤቶች የ2000 በጀት ዓመት የዓመታዊ ዕቅድ ተሰብስቦ ያዘጋጁት አመታዊ እቅድ የዕቅድ አዘገጃጀት ሥርዓትን መከተሉን በሚገባ ተገምግሞ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል ፡፡
4. በወረዳው አንድ ቀበሌ የማህበረሰብ መረጃ ማዕከል ለማቋቋም በታቀደው መሠረት በአመያ ቀበሌ የተቋቋመ ሲሆን አገልግሎት ለመስጠት ከክልል የአፈፃፀም መመሪያ እስክላክ ድረስ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል ፡፡
5. የሰቪል ሰርቢስ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በወረዳ በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ክትትል ማካሄድና ቴክንካል ድጋፍ በመስጠት የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻል ማድረግና የህዝብ አገልጋይነት ስሜት ለመፍጠር በተለያዩ መገለጫዎች የተከናወኑ ሲሆን፣
   - ❖ 100% በወረዳው ባሉ የመንግስት መ/ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስራ ላይ እንዲዉል በተደረገው ክትትልና ግምገማ በየስራ ሂደቱ በራፎች አገልግሎት ተቀባዩ በግልጽ በሚመለከትበት ቦታዎች ላይ ተለጥፎ በቀላልሉ አገልግሎት በመስጠት የመሰረታዊ የስራ ሂደት ትግበራን እንደ ስርዓትነት መትከል የሚቻልበት ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡
   - ❖ በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተገልጋይ ቅሬታ መቀበያ እና ማስተናገጃ ሥርአት በርካታ ተገልጋዬች ባሉባቸዉ ተቋማት ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማትጽ/ቤት ፣ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት እንዲሁም በቀሩት ሴ/ር በአዲሱ አሰራር መሰረት መተግበራቸዉን ክትትልና ድጋፍ እተደረገ ይገኛል፡፡

- በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ትግበራ ወቅት በምደባና ድልድል ወቅት የሚታዩ ሰራተኞች ባላመለከቱበት መመደብ፣ በድልድል ወቅት ተንሳፋፊ ሆነዉ ወደሌላ ሴ/ር መቤቶች በስትሪንግ ኮሚቴ አማካኝነት በሽግሽግ የተመደቡ ግለሰቦች ከምደባ ቡኃላ በተስተካከለ የሰራተኞች የስራ ልምድ ማነስ ምክንያት ያልደተመደቡ ሰራተኞች ሲመደቡ እኛም ካልተመደብን የሚሉ ቅሬታዎችን እያቀረቡ ቢሆንም ለቀረበዉ ቅሬታ የመፍትሄ እርምጃዎችን በመዉሰድ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ተሰርቷል።

6. በሰዉ ሃብት ሥራ አመራር በታቀደዉ እቅድ መሰረት የተከናወነ

- በበጀት አመቱ ለሰራተኞች ደመወዝ በየወሩ በመጠየቅ እንዲሁም የሥራ ማስኬጃ በጀት በአግባ አገልግሎት ላይ እንዲዉል ተደርጓል ።
- በጽ/ቤቱ በኩል የቀረበ የአንድ ግለሰብ ቅሬታ በመቀበል የግለሰብን ማህደር እስከ ጽ/ቤቱ በመሄድ የማጣራት ሥራ ከተሰራ ቡኃላ የመጨረሻ ዉሳኔ እንዲደርሰዉ ተደርጓል ።
- የ2001 ዓመት የንብረት ግዢና ወጪ ጥያቄ በአግባቡ የተፈፀመ ሲሆን የ2002 ዓ/ም ጥያቄ ቀርቧል።
- ቋሚ የቅጥር ደብዳቤየሌላቸዉ ሰራተኞች የቋሚነት ደብዳቤ በመስጠት ለሚመለከተዉ ክፍል እንዲያዉቀዉ ግልባጭ ተመዝግቧል።
- በ2001 በጀት ዓመት መገባደጃ ላይ ለለዉጥ ፕሮግራሞች የሥራ ሂደት 1 ሰዉ ተቀጥሯል።
- በዓመቱ በአንድ የጽ/ቤቱ ሠራተኞች ላይ መመሪያና ደንብ ተንተርሶ የዲሲፕሊን እርምጃ ተወስዷል ።
- ከመመሪያና ደንብ አኳያ ሠራተኞች በአግባቡ ፍቃድ መጠቀሙን ክትትል ተደረጓል
- የተመሩ ደብዳቤዎች ረቂቅ የፁሁፍ ሥራና አስተዳደራዊ ሥራዎች ተሰርቷል።
- የጡረታ ቅጥር ላልመጣላቸዉ 6 ሰራተኞች መረጃ ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተልኳል /ተወስዷል /ምላሽ እየተጠበቀ ነዉ።
- የ1 አዲስ ሰራተኛ መረጃ በማጠናቀር ለሚመለከተዉ ክፍል ለመላክ የተዘጋጀ ሲሆን የ11 ሰራተኞች የሂወተወ ታሪክ መረጃ ጥያቄ ላቀረበ ክፍል ተልኳል ።
- በሹመት ከሌላ መ/ቤት ወደ ጽ/ቤቱ የመጡ የ2 ሠራተኞች ማህደር ቀደም ሲል ከነበሩበት መ/ቤት በመጻጻፍ እንዲመጣ ተደርጓል ።

7.በፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ ከታቀዱ እቅዶች የተሰሩና የተከናወኑ ስራዎች ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ለ 2 ወላጅ አልባ ሕፃናት ለእያንዳንዳቸዉ 200x2 = 400 ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ እናትን አባት በድምሩ 2ሰዉ ለእያንዳንዳቸዉ ለአንድ እናት 300 ለአንድ አባት250 በድምሩ 550 የቡና ጠጡ ፕሮግራም የተካሄደበት ብር 263.96 የኮንዶም ስርጭት ተሰርቷል፡፡

## ያልተፈፀሙ አበይት ዝርዝር ዉጤቶች

1. አድቫንስ የኮምፒዩተር ኢንተርኔት ስልጠና ያገኙ 20 የወረዳ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች
2. በዘመናዊ መረጃ ማስተላለፍ( e-mail) ስራ የሰለጠኑ የቀበሌ መረጃ ሰራተኞች

### ጠንካራ ጎኖች ፡-

- ጽ/ቤታችን ከሌሎች ጽ/ቤቶች ጋር በቅንጅት መስራቱ
- የወረዳው አስ/ጽ/ቤት ለሚያጋጥሙን ችግሮች ከጎናችን መሆኑ
- የጽ/ቤታችን ሠራተኞች በሙሉ የሥራ ተነሳሽነት ያላቸው መሆናቸው
- ሁሉም ሠራተኞች የየወሩ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ማድረግ እና ባቀዱት እቅድ መሰረት ሥርውን ለማከናወን ጥረት ማድረጋቸው ፡፡

ደካማ ጎኖች ፡-

- በስልጠና ዙሪያ የታቀዱ እቅዶች ወቅቱን ጠብቀው ተግባራዊ ያለመሆናቸው
- ጽ/ቤታችን ከቀበሌዎች ጋር ተከታታይነት ያለው መረጃ ልውውጥ ያለማድረግ

### በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

- አንዳንድ ጽ/ቤቶች የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ስልጣንና ተግባር ያለመገንዘብ
- የኮምፒዩተር ስልጠና ስንሰጥ የኮምፒዩተር እጥረት ማጋጠም
- ለጽ/ቤት ኃላፊዎችና አመራሮች ስልጠና ለመስጠት በተለያዩ ወቅታዊ ሥራዎች ምክንያት ችግር መፈጠሩ ወደ ቀበሌዎች የሚሄዱ ደብዳቤዎች ወቅታዊ ምላሽ ያለማግኘት
- የበጀት እጥረት ያጋጠመን መሆኑ

### የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ስልጣንና ተግባር ለማሳወቅ የፍትህ አካላትና የሲቪል ሰርቪስ ኦፊሰሮችን ስብሰባ በመጥራት መመሪያዎችና ደንቦችን በማንበብና በመተማመን እየሰራን ሲሆን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲገጥመን ከወረዳው

አስተዳደር ድጋፍ እንዲደረግልን በማድረግ በካቢኔ ስብሰባ በጋራ በመወያየት ችግሩን እየፈታን ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ ፡፡

- ኮምፒዩተር ያላቸው ጽ/ቤቶች እንዲተባበሩን በመጠየቅ በታቀደው መሰረት ስልጠናው ተሰጥቷል ፡፡
- ለጽ/ቤት ኃላፊዎችና አመራሮች የሚሰጡ ስልጠናዎች አመቺ በሆነ ጊዜ ተመቻችተው እንዲሰጡ ከወረዳው አስተዳደር ጋር ተወያይተናል ፡፡
- የቀበሌ አመራሮች የልዩ ወረዳውን አቅም ግንባታ የሥራ ድርሻ ለይተው እንዲያወቁ ወደ መስክ የሚሄዱ አመራሮችና ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ እንዲሠሩና የጽ/ቤታችን ባለሙያዎችም ወደ ቀበሌ ገብተው ለአመራሮች ስልጠና እንዲሰጡ በማድረግ መልካም ግንኙነት እየፈጠርን እንገኛለን ፡፡
- በቀጣይ የበጀት ዓመት የበጀት ችግር እንዲቀረፍ ማሣሰብ ፡-

## ለወደፊቱ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ፡-

- በልዩ ወረዳው ያሉ 42 ውም ቀበሌዎች በመልካም አስተዳደርና በሌሎችም አቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ለማድረግ የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ፣ ለሌሎች ሴክተር ጽ/ቤት እና ሌሎችም ሴክተር መ/ቤቶች እገዛ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ፡፡
- የክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮም የተለያዩ ቁሳቁሶች ፣ ኮምፒዩተር ፋክስ እና የክልል ባለሙያዎች እገዛ በማድረግ አቅማችንን ቢያጎልብት በጽ/ቤታችን የተሻለ አሰራር ይፈጠራል ፡፡
- ሪፖርቱን ያጠናቀረው ባለሙያ

ስም -----------------------------------

የሥራ ድርሻ -----------------------------

ፊርማ ------------------------------------

ቀን /ወር /ዓ/ም-------------------------

**ያረጋገጠው ኃላፊ ስም**

ስም -----------------------------------

የሥራ ድርሻ ----------------------------

ፊርማ ------------------------------

ቀን /ወር /ዓ/ም----------------------